# ግልጽ አደጋ በሎስ አንጀለስ አብያተ ክርስቲያናት

ታዬ ብርሀኑ

የሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን የምትታወቀው ገዳማዊና የወንጌል ፈርጥ የሆኑ ካህናት፣ ከዋክብት የሆኑ መዘምራንና በወንጌል የታነጹ ምዕመናን አቅፋ አገልግሎት በመስጠት ነው። ተግባሯ በወንጌል ፋና ወጊነት፣ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን የትም ብትገኝ አንድ እንደሆነች በማመን አገልጋዮቿን በተለያዩ ክፍለ አህጉራት እና አገራት በማሰማራት ዓለም አቀፋዊ አገልግሎት በመስጠት ነው።ጃንሜዳ በሎስ አንጀለስ በሚል በስደት የሚገኙትን አባቶችና ምዕመናን በአንድነት በሞገስ የሚቆሙበትን መድረክ በማዘጋጀት ላለፉት 13 ዓመታት በስደት ለምትገኘው ቤተክርስቲያን የበረከት ምክንያት ሆናለች፤ እንደዚሁም በአቡነ መልኬጸዴቅን እና በስደት ላይ በሚገኙት ታላላቅ የቤተክርስቲያን አባቶችን ላይ ፣ ማህበረ ቅዱሳን በተባለው የወንድሞች ከሳሽ አማካይነት የተሰበቀውን ጦር እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ መክታለች።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በስደት ያሉትን አባቶችና መላውን ዓለም ያስተባበሩበትን ወንጌል አገልግሎት ለመበታተን በተቀነባበረ ሁኔታ ዘመቻ ተከፍቶአል። በከፍተኛ ደረጃ ለዚህ ዓላማ እየተንቀሳቀሰ ያለው ሥውር አካል እነ አባ ወልደ ትንሣኤን እስከማሳሰር አቡነ መልከ ጼዴቅን በቅዱስ ፓትርያርኩን ላይ በተቃራኒነት እንዲቆሙ እስከማድረስ ገፋፍቷል፤ አሁን ደግሞ የህጋዊ ሲኖዶስ ታማኝና ትልቅ የድጋፍ ሃይል(base) ወደ ሆነው የሎስ አንጀለስ ቤተ ክርስቲያን ዓይኑን ዘወር አድርጎአል።

በተለይም በዚህ ሲኖዶሱን በማፈራረስ ተልእኮ ውስጥ ዋናውን ሚና የሚጫወቱት በሎስ አንጀለስ የሚገኙት አባ ጽጌ፤ በቤተ ክርስቲያናቸው አውደ ምህረት ላይ ቆመው ዓመታት ካስቆጠረ የመለያየፊት በኋላ በእርቅና በሰላም የኖሩትን ሁለቱን የሎስ አንጀለስ አብያተ ክርስቲያናት የሚለያይ የጥላቻ ዘር ዘርተዋል። አባ ጽጌ በዚሁ ነውረኛ ንግግራችው የሊቀ ጳጳስና የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ካህናትን ስም ዕየጠሩ "የተወገዙትን የኦክላንድ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ሄደው ስላገለሉ ቀኖናን አስመልክቶ ከድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያንና ከካህናቱ ጋር የተለያየን ነን፣ ህጋዊውን ሲኖዶስ ከመሰረቱት ሶስቱ አባቶች ሁለቱ አባቶች ሞተዋል አንዱ ናቸው የቀሩን እሳቸውም የ90 ዓመቱ አዛውንት ብጹዕ አቡነ መልከጸዴቅ ናቸው ዕርሳቸውን ተንከባከቡ ። አቡነ ያዕቆብና አባ ወልደትንሣኤ የመንበረ ፓትርያርኩ አድሳቱ ሳይጠናቀቅና ሳይባረክ ቅዱስ ፓትርያርኩን ሠርቀው ወደ ተገዛው መኖሪያ ቤት አስገብተዋል" በማለት የድንግል ማርያም ካህናትን በመክሰስ እንዳስለመዱት ፓትርያርኩን በማዋረድ ምዕመናንን ባስገረመና ባስቆጣ ሁኔታ ከምህረት አደባባይ ላይ ቆመው መለያየትን ሲሰብኩ ውለዋል።ይህ አባ ጽጌ ያቀጣጠሉት የመለያየት እሳት ዳግም ሁለቱን የሎስአንጀለስ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ሊበርድ ወደማይችል የመለያየት ቁልቁለት ላይ እንዲቀመጥና የሲኖዶሱ ፈርጥ የሆኑትን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ለያይቶ ሲኖዶሱን ለማዳከም ነው።

ይህ የአባ ጽጌ የመለያየት መርዝን ከሥር ከመሠረቱ መንግሎ ለመጣል ቅዱስ ሲኖዶሱና የዚህን የሲኖዶሱን አንድነት የሚፈልጉ ሁሉ እውነቱን እንዲያስታውሱ የሚከተሉትን እውነቶች ማሳየት እፈልጋለሁ።

## ቅዱስ ፓትርያርኩን የመጋፋት ሂደት

አባ ጽጌና ቡድናቸው ሲኖዶሱን ለማዳከም ቍልፍ ያሉት ነገር ቢኖር የቅዱስ ፓትርያርኩን ሥልጣን መጋፋትና ቀስ በቀስ የሲኖዶሱን ሕጋዊነት ማሳጣት ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የኦክላንድ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ፓትርያርኩ ድጋፍ አግኝቶ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ቤተ ክርስቲያን ነው። ያለምንም ተቀናቃኝና ተቆጣጣሪ ለ25 ዓመት በሥልጣን ላይ የቆየውን ቦርድ ሥልጣን ለማስጠበቅ ካህኑን ፣ የኦዲት ኮሚቴውንና ከ250 በላይ ምዕመናንን ያጠቃለለው የጅምላ ውግዘት አባቶች ባስመቀጡልን የቀኖና መስፈርት እንዳልተከናወነ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን በሲኖዶሱ ጉባኤ ላይ በግልጥ ለአቡነ መልከ ጼዴቅ ነግረዋቸዋል፤ ለቤተ ክርስቲያኑም የእውቅና ደብዳቤ የጻፍኩት እኔ ነኝ ብለው ለጉባኤው ሁሉ አስታውቀዋል። በዚያን ወቅት በዚያ ጉባኤ ላይ ስለ ተከናወነው አሳፋሪ ድርጊት በሌላ ቀን እመለሳለሁ። አባ ጽጌ ይህን የፓትርያርኩን እውቅና ግን ከአንድ ቄስ በማይጠበቅ ድፍረት " ፓትርያርኩ ሥልጣናቸው ከሲኖዶሱ ሥር ነው" በማለት ከዋሽንግተን ዲሲ ካሉትና ቅዱስ ፓትርያርኩን በአደባባይ ከሚሳደቡ ወንድሞቻቸው የሰሙትን ዜማ አስተጋብተዋል።

## <u>ለመሆኑ ከተወገዘ ጋር እየቀደሰ ያለ ማን ነው?</u>

ውግዘትን በተመለከተ፡- ለመሆኑ አባ ጽጌ ከመቼ ወዲህ ነው "የውግዘት ጠባቂና ተቆጣጣሪ" የሆኑት? እርሳቸው አይደሉም እንዴ የአዲስ አበባው የወያኔ ሲኖዶስ ዋና ተወካይ ከሆነውና የሎስ አንጀለስን ሕዝበ ክርስቲያን ከከፋፈለው ከቄስ ሙሴ ጋር እጅና ጓንት ሆነው የሚሰሩት። እጅግ የሚገርመው ደግሞ የገዛ ቤተ ክርስቲያናቸው ምዕመናን እንኳ ይህ አሰራር አልዋጥላቸው ብሎ በጽሁፍ (ፔቲሽን) መልክ  ከቄስ ሙሴ ጋራ ካህናቶቻቸው እንዳያገግሉ ጥያቄ ቢያቀርቡ አባ ጽጌ አይደሉም እንዴ አሻፈረኝ በማለት "መቅደሱ የኛ የካህናት ነው አያገባችሁም"ብለው መልስ የሰጡት። ቄስ ሙሴ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ አባ ጳውሎስና/ማትያስን ራሳችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አቡነ መርቆሬዎስን በቅዳሴያችው ይጠራሉ። ሁለት ባላ ትከል አንዱ ቢፈርስ በአንዱ ተንጠልጠል ማለት ይሄ ነው። ወደ ውስጥ ገባ ካልን ደግሞ ሕግ ተከትለው ለቅዱስ ፓትርያርኩ በማስታወቅ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ሥልጣኑን የያዙበት የዲሲ ገብርኤል ካህን ጋር እየቀደሱ ያሉት ናቸው ስለውግዘት የሚነግሩን?

## <u>ስለ ሲኖዶሱ አመሠራረት የአባ ጽጌ አዲሱ ታሪክ</u>

አባ ጽጌ በዚህ ጉደኛ ንግግራቸው ላይ የቅዱስ ሲኖዶስ ምስረታ አስመልክቶ የቅዱስ ፓትርያርኩን ሕጋዊ መሪነት ሚና ለማሳጣትና የሌሎችን ለማግዘፍ የነ ዶ/ር ነጋን ነጠላ ዜማ አስተጋብተዋል። አቡነ ዜና፤አቡነ ይስሐቅና አቡነ መልኬጸዴቅ የቅዱስ ፓትርያርኩን ፍቃድ እስኪያገኙ ድረስ ስብሰባቸው ማኅበረ ካህናት ይባል ነበር። ምክንያቱም ያለ ፓትርያርኩ መሪነት ህጋዊ ሲኖዶስ ስለማይባል። በመሆኑም ቅዱስ ፓትርያርኩ በስደት ኬንያ ሰለነበሩ በጊዜው እንደራሴአቸው ለነበሩት ለብጹዕ አቡነ ዜና ፍቃድ በመስጠታቸው ነው ህጋዊ ሲኖዶስ ሊመሰረት የቻለው።ይህንን እውነታ ካላወቁ በጊዜው ከነበሩት አባቶች ጠይቆ መረዳት አስተዋይነት ነው። ይህ ሁሉ ግን  "ሲኖዶሱን የመሠረትነው እኛ ነን እርስዎን አንፈልግም" ተብሎ በአደባባይ ለቅዱስ ፓትርያርኩ በኦሀዮ ሲኖዶስ የተነገረውን ለማጽደቅ ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ቅዱስ ፓትርያርኩን አንፈልግ ተብሎ በአዋጅ ይነገርና የሚለየው ይለይ። የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ የተቃወምነው ሕግ ጣሰ ብለን እንጂ የአንዳንዶችን ከፍታና ክብር ለማስታመም አልነበረም። ከሁሉ የሚያሳዝነው ለእርሳቸው እዚህ መድረስ ባለውለታ የነበሩትን አቡነ ይስሐቅን ብዙ በደከሙበት መድረክ ላይ አዋርደው የሰደዱአቸው አባ ጽጌ ሆነው ሳለ ዛሬ ለመጠቀሚያ ስማቸውን ያነሳሉ፤ ይህ ጉዳይ ታላቁ አባት አባ መንግሥቱ ዘወትር የሚያለቅሱበት እንደነበረ የቅድስት ማርያም ሰዎች በሚገባ ያውቃሉ።

## <u>ሲኖዶሱ የሚመራው በማነው?</u>

የአባ ጽጌ እና የመሰሎቻቸው ንግግርን በጥንቃቄ ለአደመጠው ሰው  የሚያስተላልፉት ምሥጢራዊ መልእክት አለ። መልእክታቸው ቅዱስ ፓትርያርኩ ሲኖዶሱን መምራት እንደማይችሉ፣ እንደማያነቡ፣ የማያነቡትን እንደሚፈርሙ፣ በራሳቸው ምንም መወሰን እንደማይችሉ ነው። ይህ ደግሞ የዛሬ 22 ዓመት ገደማ የነአባ ጽጌ አለቆች ቅዱስ ፓትርያርኩን ለማውረድ የሰጡት ምክንያት ነው እንጂ አዲስ ግኝት አይደለም። ስለመንበረ ፓትርያርኩ አባ ጽጌ በአውደ ምሕረቱ ሲናገሩ ለሰማቸው የሚናገሩት ስለፓትርያርክ አይመስልም። ተሠርቀው የሚወሰዱት ቅዱስ ፓትርያርኩ ዕቃ ናቸው፤ አዲስ ወደ ተገዛው መንበረ ፓትርያርክ  እንዴትና በማን ትእዛዝ እንደተገባ ቅዱስ ፓትርያርኩ ራሳቸው በወቅታዊ መልእክታቸው ስላዳሰሱት መልዕክቱን ከዚህ ጽሁፍ ጋር ተያይዟል። እንደተለመደው እርሳቸው አልጻፉትም ካላሉን በቀር።  እንግዲህ ጉዳዩ ቅዱስ ፓትርያርኩ ማዝዝም መባረክ አይችሉም ከሆነ የአባ ጽጌን እና ከእርሳቸው ጋር ያሉትን ቡድኖች አካሄድ ህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ሊመረምረው ይገባል።

## <u>የተቀነባበረው ሤራ በአፍ ወለምታ ሲጋለጥ</u>

ልብ ሊለን የሚገባው ነገር በሎስ አንጀለስ አውደ ምሕረት ቆመው የሚከፋፍሉት አባ ጽጌ፤ በሲኖዶስ ጉባኤ ላይ ሊቃነ ጳጳሳትን የሚዘልፈው ዲያቆን አንዱዓለም፤ ቅዱስ አባታችንን ዲሲ ገብርኤል ላይ ሲወርፍ የነበረው ዲያቆን ፍሬስብሃት እና ታላቁን መምህር አባ ወልደ ትንሣኤን ወደ ጉባኤው እንዳይገቡ መልሷችው ካረፉበት ቦታ በአባ ጽጌ አማካይነት በስልክ አስጠርቶ በሐሰት ያሳሰረው ዶ/ር ነጋ  በአንድ የጥፋት መስመር ሃይል መሰለፋችው ነው። ንግግራቸውንም ለሰማው ከአንድ ተጽፎ ከተሰጣቸው ወረቀት የሚያነቡ ይመስላሉ። ዓላማቸውም አንድ ነው፤ ቅዱስ ፓትርያርኩን መዋጋት ነው። ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ሌላው ነገር ደግሞ በተለያየ መንገድ አዲስ አበባ ካለው ሲኖዶስ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆናቸው ነው።

ዲያቆን አንዱዓለም የዲሲውን ዲያቆን ፍሬ ስብሃት ለህዳር ሚካኤል ወደ ዳላስ ጋብዞት እንደነበረና ከዳላስ አካባቢ የመጣው መረጃ ያስረዳል ተያይዞ በደረሰን መረጃ ስንት የወንጌል ሰባክያን ባሉበት እንዴት የወያኔ ካድሬና የወንድሞች ከሳሽን አንዱዓለምና ቦርዱ ሊጋብዝ ቻሉ የሚል ጥያቄ በዳላስ ሚካኤል ምዕመናን ዘንድ ተጭሯል ። አባ ጽጌም በሎስ አንጀለስ የጥምቀት በዓል ላይ ለዲያቆን ፍሬ ስብሃት በመሪ የወንጌል ሰባኪነት መድረክ ሊሰጡት በመርሃ ግብሩ ላይ እንደተካተተ ከሎስ አንጀለስ የመጣው መረጃ ያሳያል። በአባ ጽጌ ሃላፊነት የተዘጋጀው የወንጌል መርሃ ግብር ለመጀመሪያ ጊዜ የሎስ አንጀለስ የድንግል ማርያም ካህናትና ታዋቂ ሰባክያንን እንዳላካተተ መረጃው ያሳያል። ወንጌል የታጠቀው የሎስአንጀለስ ምዕመናን የማህበረ ቅዱሳኑ ጎበዝ አለቃ ዳንኤል ክብረትን በውርደት ባስተናገደው መልኩ ዲያቆን ፍሬስብሃትን እንደሚቀበለው ይጠበቃል።

## ማጠቃለያ

ሰላምን እየሰበኩ ጦርን መሰበቁ ስለ ፍቅር እየተናገሩ ጥላቻን መዝራት በቶሎ ሊቆም ይገባል።አባ ጽጌ የይቅርታና የሰላም ሰው ላለመሆናቸው በቅርቡ ስለ እርቅና ሰላም ከሚኖሩበት ክፍለ ከተማና ሀገራት ሊያነጋግሩአቸው የሄዱትን ሊቀ ጳጳስና ካህናት አሻፈረኝ ብለው የሰላሙን በር ዘግተው እንደሸኙአችው ይታወቃል። እንዲያውም በግለሰቦች አሳሳቢነትና የአውሮፕላን ቲኬት ወጪ ለእርቅ የመጡትን አባቶች ጊዜ ሳይሰጡ መድረክ አገኘሁ በማለት የግል ጥላቻን አውደ ምህረት ላይ እያወጡ ምዕመናንን ውዝግብ ውስጥ መክተት እጅግ የሚያሳዝን ተግባር መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ መገንዘብ አለበት። እንዲህ ዓይነቱም ሰው ለቦታው የማይመጥኑ ከሰው ጋር ተደማምጠውና ተግባብተው መስራት የማይችሉ እኔ ያልኩት ካልሆነ ባይና እኩራፊ ስለሆኑ ቃሉም በትዕቢት ተወጥሮ እንዳይወድቅ እንዲህ ዓይነቱን ሰው ሹመት አትስጠው ስለሚል፤ የወደዱትን እየጠቀሙ የጠሉትን እየጎዱ የስልጣን ጥማታችውን እየተውጡበት ከሚገኙበት ኃላፊነት ቅዱስ ሲኖዶሱ በአስቸኳይ ሊያነሳችው ይገባል እላለሁ ።

ቸር እንሰንብት።